## የገንዘብ ሚኒስቴር

# ከገቢ ግብር ነፃ የተደረጉ ገቢዎች አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 1/2011

በኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር
ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.2
Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No. 2

መጋቢት 2011 ዓ/ም
አዲስ አበባ

## ከገቢ ግብር ነፃ የተደረጉ ገቢዎች አፈጻጸም
## መመሪያ ቁጥር 1/2011

### 1. አውጪው ባለሥልጣን

የገንዘብ ሚኒስትሩ በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 አንቀጽ 65/1/ሀ እና አንቀጽ 99/2/ በተሰጠው ሥልጣን መሰረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### 2. አጭር ርእስ

ይህ መመሪያ ከገቢ ግብር ነፃ የተደረጉ ገቢዎች አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 1/2011 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 3. ትርጓሜ

በፌዴራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 ወይም በፌዴራል የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 ትርጉም የተሰጠው ቃል በዚህ መመሪያ ውስጥ ጥቅም ላይ የዋለ እንደሆነ በታክስ አስተዳደር አዋጁ ወይም በገቢ ግብር አዋጁ የተሰጠውን ትርጉም ይይዛል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ ፡-

ሀ. **"ደመወዝ"** ማለት በአንድ የስራ ደረጃ ላይ የተመደቡ ሠራተኞች ለሚሰጡት አገልግሎት በቀጣሪው የሚከፈል ክፍያ ሲሆን አበል እና ጥቅማ ጥቅሞችን አይጨምርም፡፡

ለ. **"የትራንስፖርት አበል"** ማለት በቀጣሪው እና በተቀጣሪው መካከል በተደረገ ውል ውስጥ በግልጽ የተመለከተ እና ተቀጣሪው ከመኖሪያ ቤቱ ወደ ሥራ እንዲሁም ከሥራ ቦታው ወደ መኖሪያ ቤቱ ለመጓጓዝ እንዲሁም ተቀጣሪው ሥራውን ለማከናወን መደበኛ የሥራ ቦታው በሚገኝበት ከተማ ውስጥ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ለመዘዋወር የሚያስፈልገው የትራንስፖርት ወጪ ለመሸፈን በቀጣሪው የሚከፈል አበል ነው፡፡

ሐ. **"የውሎ አበል"** ማለት አንድ ተቀጣሪ የተቀጠረበትን ሥራ ለማከናወን መደበኛ የሥራ ቦታው ከሚገኝበት ከተማ ውጪ ከ25 ኪሎ ሜትር በላይ ርቆ በሚሄድበት ጊዜ ለመኝታ፣ ለምግብ፣ ለመጠጥና ለተዛማጅ ወጪዎች የሚከፈል አበል ነው፡፡

...thiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No. 2

# ከገቢ ግብር ነፃ የተደረጉ ገቢዎች አፈጻጸም
## መመሪያ ቁጥር 1/2011

1. **አውጪው ባለሥልጣን**

የገንዘብ ሚኒስትሩ በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 አንቀጽ 65/1/ሀ እና አንቀጽ 99/2/ በተሰጠው ሥልጣን መሰረት ይህን መመሪያ አውጥቷል።

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

2. **አጭር ርእስ**

ይህ መመሪያ ከገቢ ግብር ነፃ የተደረጉ ገቢዎች አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 1/2011 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

3. **ትርጓሜ**

በፌዴራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 ወይም በፌዴራል የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 ትርጉም የተሰጠው ቃል በዚህ መመሪያ ውስጥ ጥቅም ላይ የዋለ እንደሆነ በታክስ አስተዳደር አዋጁ ወይም በገቢ ግብር አዋጁ የተሰጠውን ትርጉም ይይዛል። ከዚህም በተጨማሪ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ ፡-

ሀ. **"ደመወዝ"** ማለት በአንድ የስራ ደረጃ ላይ የተመደቡ ሠራተኞች ለሚሰጡት አገልግሎት በቀጣሪው የሚከፈል ክፍያ ሲሆን አበል እና ጥቅማ ጥቅሞችን አይጨምርም።

ለ. **"የትራንስፖርት አበል"** ማለት በቀጣሪው እና በተቀጣሪው መካከል በተደረገ ውል ውስጥ በግልጽ የተመለከተ እና ተቀጣሪው ከመኖሪያ ቤቱ ወደ ሥራ እንዲሁም ከሥራ ቦታው ወደ መኖሪያ ቤቱ ለመጓጓዝ እንዲሁም ተቀጣሪው ሥራውን ለማከናወን መደበኛ የሥራ ቦታው በሚገኝበት ከተማ ውስጥ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ለመዘዋወር የሚያስፈልገው የትራንስፖርት ወጪ ለመሸፈን በቀጣሪው የሚከፈል አበል ነው።

ሐ. **"የውሎ አበል"** ማለት አንድ ተቀጣሪ የተቀጠረበትን ሥራ ለማከናወን መደበኛ የሥራ ቦታው ከሚገኝበት ከተማ ውጪ ከ25 ኪሎ ሜትር በላይ ርቆ በሚሄድበት ጊዜ ለመኝታ፣ ለምግብ፣ ለመጠጥና ለተዛማጅ ወጪዎች የሚከፈል አበል ነው።



Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No. 2

መ. **"በሥራ ሁኔታ አስቸጋሪነት ምክንያት የሚከፈል አበል"** ማለት የሥራ ሁኔታው ለጨረር፣ ለበሽታ፣ ለኬሚካል ልቀት ወይም ብክለት፣ ለንፁህ አየር እጥረት፣ ለከፍተኛ ሙቀት፣ ለከፍተኛ ቅዝቃዜ የሚያጋልጥ ወይም በማናቸውም ሌላ ምክንያት በተቀጣሪው ጤናና ደህንነት ላይ ጉዳት ሊያደርስ የሚችል መሆኑን ከግምት ውስጥ በማስገባት የሚከፈል አበል ነው፡፡

ሠ. **"በሥራ ቦታው አስቸጋሪነት ምክንያት የሚከፈል አበል"** ማለት የሥራ ቦታው የሚገኝበት ከተማ ከፍተኛ ሙቀት ያለው ወይም ለኑሮ አስቸጋሪ በመሆኑ ወይም በሌላ ተመሳሳይ ምክንያት በተቀጣሪው ላይ ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት ከግምት ውስጥ በማስገባት የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ባወጣው መመሪያ መሠረት የሚከፈል አበል ነው፡፡

ረ. **"አዋጅ"** ማለት የፌደራል የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 ነው፡፡

ሰ. **"ደንብ"** ማለት የፌደራል የገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 410/2009 ነው፡፡

ሸ. **"ባለሥልጣን"** ማለት የገቢዎች ሚኒስቴር ወይም የአዲስ አበባ ወይም የድሬዳዋ አስተዳደር ገቢዎች ባለስልጣን ነው፡፡

## 4. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ በአዋጁ እና በደንቡ ከገቢ ግብር ነፃ በተደረጉ ገቢዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

# ክፍል ሁለት
# አበል እና ሽልማት ከግብር ነፃ የሚደረግበት ሁኔታ

## 5. <u>የትራንስፖርት አበል እና የመጓጓዣ ወጪ</u>

1. በስራ ባህሪው ምክንያት ሥራውን ከቦታ ወደቦታ በመዘዋወር የሚያከናውን ተቀጣሪ ለአንድ ወር ጉዞ የሚከፈለው የትራንስፖርት አበል ከገቢ ግብር ነፃ የሚደረገው ከጠቅላላ የወር ደመወዙ ከአንድ አራተኛ (1/4) ባልበለጠ መጠን ብቻ ነው፡፡ ይሁንና የተቀጣሪው ጠቅላላ የወር ደመወዝ አንድ አራተኛ ከብር 2200 የሚበልጥ ሲሆን ከግብር ነፃ የሚደረገው የትራንስፖርት አበል በማንኛውም ሁኔታ ከብር 2200 ሊበልጥ አይችልም፡፡

2. አንድ ተቀጣሪ በስራ ባህሪው ምክንያት በመዘዋወር ለሚሰራው ስራ ለነዳጅ ወጪ የሚከፈለው ጥሬ ገንዘብ ለትራንስፖርት አበል እንደተከፈለ ተቆጥሮ ከገቢ ግብር ነጻ የሚደረገው ከጠቅላላ የወር ደመወዙ ከአንድ አራተኛ (1/4) ባልበለጠ መጠን ብቻ ነው፡፡ ይሁንና የተቀጣሪው ጠቅላላ የወር ደመወዝ አንድ አራተኛ ከብር 2200

Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No. 2

የሚበልጥ ሲሆን ከግብር ነፃ የሚደረገው የነዳጅ ወጪ በማንኛውም ሁኔታ ከብር 2200 ሊበልጥ አይችልም፡፡

3. አንድ ተቀጣሪ ከመኖሪያ ቤቱ ወደ ስራው ቦታ እንዲሁም ከስራው ቦታ ወደ መኖሪያ ቤቱ የሚጓጓዝበት የመሥርያ ቤቱ የትራንስፖርት ሰርቪስ ቢቀርብም ባይቀርብም ለዚህ ዓይነቱ የትራንስፖርት አበል ከገቢ ግብር ነፃ የሚደረገው ከብር 600 ባልበለጠ መጠን ብቻ ነው፡፡

4. አንድ ተቀጣሪ ከመኖሪያ ቤቱ ወደ ስራው ቦታው እንዲሁም ከስራው ቦታ ወደ መኖሪያ ቤቱ ለመሄድ ለነዳጅ ወጪ በጥሬ ገንዘብ የሚከፈለው የትራንስፖርት አበል ከገቢ ግብር ነፃ የሚደረገው ከብር 600 ባልበለጠ መጠን ብቻ ነው፡፡

5. አንድ ተቀጣሪ ሥራውን ለማከናወን መደበኛ የሥራ ቦታው ከሚገኝበት ከተማ ውጪ ሲንቀሳቀስ ለመጓጓዣ ወጪ የሚሰጠው ክፍያ ከግብር ነፃ ሊሆን የሚችለው በስራ ላይ ባለው የትራንስፖርት ታሪፍ ወይም በሚያቀርበው ማስረጃ ላይ የተመሰረተ ሆኖ ከከፈለው የአየር፣ የውሃ እና የየብስ ትራንስፖርት የአገልግሎት ዋጋ ሊበልጥ አይችልም፡፡

6. አንድ የውጭ አገር ዜጋ ሥራን ለማከናወን ወደኢትዮጵያ ሲመጣ እና የውል ዘመኑን ጨርሶ ከሀገር ሲወጣ የሚከፈለው የትራንስፖርት ወጪ ከግብር ነፃ ሊሆን የሚችለው በተፈጸመው የቅጥር ውል መሰረት እና የአየር፣ የውሃ እና የየብስ ትራንስፖርት አገልግሎት ዋጋ ታሪፍ መሠረት ሆኖ ከግብር ነፃ የሚሆነው ለግል መገልገያ ዕቃዎቹ የሚከፈለው የጭነት ሂሳብ ከ300 ኪሎ ግራም ሊበልጥ አይችልም፡፡

7. አንድ ግብር ከፋይ ከመደበኛ መኖሪያ ቦታቸው ርቀው ሥራቸውን የሚያከናውኑ ሠራተኞች ቤተሰባቸውን ለመጠየቅ የሚያደርጉትን ጉዞ ወጪ የሚሸፍን በሚሆንበት ጊዜ የዚህ ዓይነቱ ወጪ ከግብር ነፃ ሊሆን የሚችለው በተፈፀመው የቅጥር ውል ውስጥ ቀጣሪው ይህ ግዴታ ያለበት ሆኖ ሲገኝ ነው፡፡ ሆኖም ለዚህ ዓይነቱ ጉዞ የሚከፈለው ወጪ ከግብር ነፃ የሚደረገው በአንድ የግብር ዓመት ከሁለት የደርሶ መልስ ጉዞ ባልበለጠ መጠን ብቻ ነው፡፡

6. <u>የውሎ አበል</u>፣

1. በሀገር ውስጥ ለሚደረጉ ጉዞዎች የሚከፈል የውሎ አበል፣

ሀ. አንድ ተቀጣሪ የሚከፈለው የቀን የውሎ አበል ከገቢ ግብር ነፃ የሚደረገው ከብር 500 ወይም ከደሞዙ 4% ከሁለቱ ከፍተኛ ከሆነው መጠን ባልበለጠ ብቻ ነው፡፡

Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No. 2

ለ. ለዚህ ንኡስ አንቀጽ ለፊደል ተራ ሀ አፈጻጸም አንድ ተቀጣሪ የአልጋ አበል ያስገደብ ወይም በተወሰነ ገደብ በደረሰኝ የሚወራረድለት ከሆነ በደረሰኙ መሠረት ለአልጋ የተከፈለው ገንዘብ ከግብር ነፃ የሚደረግ ሲሆን ለቁርስ፣ምሳ፣ እራት እና የመሳሰሉ ወጪዎች የሚሰጠው የውሎ አበል ከግብር ነጻ ሊደረግ የሚችለው ከብር 300 ወይም ከደሞዙ 2.5% ከሁለቱ ከፍተኛ ከሆነው መጠን ባልበለጠ ብቻ ነው፡፡

ሐ. ለማናቸውም ድርጅት ስራ አስኪያጅ ወይም ምክትል ስራ አስኪያጅ የሚከፈለው የውሎ አበል ከግብር ነፃ የሚደረገው ከብር 1000 ወይም ከወርሓዊ ደሞዙ 5 በመቶ ከፍተኛ ከሆነው መጠን ባልበለጠ ብቻ ነው፡፡

መ. ለዚህ ንኡስ አንቀጽ ለፊደል ተራ ሐ አፈጻጸም አንድ ስራ አስኪያጅ ወይም ምክትል ስራ አስኪያጅ የአልጋ አበል ያስገደብ ወይም በተወሰነ ገደብ በደረሰኝ የሚወራረድለት ከሆነ በደረሰኙ መሠረት ለአልጋ የተከፈለው ገንዘብ ከግብር ነፃ የሚደረግ ሲሆን፣ ለቁርስ፣ ምሳ፣ እራት እና ለመሳሰሉ ወጪዎች የሚሰጠው የውሎ አበል ከገቢ ግብር ነጻ የሚደረገው ከብር 600 ወይም ከወርሓዊ ደሞዙ 3 በመቶ ከፍተኛ ከሆነው መጠን ባልበለጠ መጠን ብቻ ነው፡፡

2. ወደ ውጪ ሀገር ለሚደረጉ ጉዞዎች የሚከፈል የውሎ አበል፣

ሀ. አንድ ተቀጣሪ የተቀጠረበትን ስራ ለማከናወን ወደ ውጭ ሀገር ለሚያደርገው ጉዞ የሚከፈለው የውሎ አበል ከገቢ ግብር ነጻ የሚደረገው መንግስት ከተሿሚዎች ውጪ ለሌሎች ተቀጣሪዎቹ ከወሰነው የውሎ አበል ልክ ባልበለጠ ብቻ ነው፡፡

ለ. የማናቸውም ድርጅት ሥራ አስኪያጅ ወይም ምክትል ሥራ አስኪያጅ ከድርጅቱ ስራ ጋር በተገናኘ ወደ ውጭ ሀገር ለሚያደርገው ጉዞ የሚከፈለው የውሎ አበል ከገቢ ግብር ነጻ የሚደረገው መንግስት ከተሿሚዎች ውጪ ለሌሎች ተቀጣሪዎቹ በወሰነው የውሎ አበል ልክ ላይ 20 በመቶ ተጨምሮበት ይሆናል፡፡

3. የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ ቢኖርም በሀገር ውስጥ ለሚደረግ የስራ እንቅስቃሴ የኮንስትራክሽን ማሽነሪ ኦፕሬተሮች የሚከፈል የውሎ አበል ከ25 ኪ.ሜ ባነሰ ወይም በበለጠ ርቀት ቢሆንም የተከፈለው የውሎ አበል ከግብር ነፃ ይሆናል፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2 እና 3 የተደነገገው ቢኖርም የመንግስት መስሪያ ቤት ለተሻሚዎች እና ለተቀጣሪዎቻቸው ከመደበኛ የስራ ቦታቸው ውጪ ከ25 ኪሎሜትር በላይ ርቀው በመሄድ ለሚያከናውኑት ስራ የሚከፍሉት የቀን ውሎ አበል ሙሉ በሙሉ ከግብር ነፃ ተደርጓል፡፡

5. ለዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 5 አፈፃፀም፡-



Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation N. 2

1. "የመንግስት መስሪያ ቤት" የሚለው ሀረግ በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ የተሰጠውን ትርጉም ይይዛል፡፡

2. 25 ኪሎ ሜትር የሚለካው ከከተማው አስተዳደር ማዘጋጃ ቤት ወሰን ጀምሮ ሲሆን ማዘጋጃ ቤት የሌለው ከሆነ እንደ የሁኔታው ከከተማ አስተዳደር ወይም ከቀበሌ አስተዳደር ወሰን ጀምሮ ተቀጣሪው እስከሚንዝበት ቦታ ድረስ ያለው ርቀት ነው፡፡

## 7. በስራ ቦታው አስቸጋሪነት ምክንያት ለተቀጣሪ የሚከፈል አበል

1. በስራ ቦታው አስቸጋሪነት ምክንያት የሚከፈል አበል ከግብር ነፃ ሊሆን የሚችለው የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ባወጣው መመርያ የዚህ ዓይነቱ አበል እንዲከፈልባቸው ለተፈቀደ አካባቢዎች እና ከሚፈቀደው የአበል መጠን ያልበለጠ ይሆናል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 የተደነገገው በሲቪል ሰርቪስ አዋጅ ለማይተዳደር የመንግስት መስርያ ቤት፣ የመንግስት የልማት ድርጅት፣ መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት፣ የግል ድርጅት ተቀጣሪ ወይም ሌላ ማንኛውም ተቀጣሪ ወይም ተሿሚ በሥራ ቦታው አስቸጋሪነት ምክንያት የሚከፈል አበል ላይ በተመሳሳይነት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## 8. በስራ ሁኔታው አስቸጋሪነት ምክንያት ለተቀጣሪ የሚከፈል አበል

1. በሥራ ሁኔታ አስቸጋሪነት ምክንያት የሚከፈል አበል ከግብር ነፃ ሊሆን የሚችለው የሚመለከተው የመንግስት መስርያ ቤት ለእነዚህ ሠራተኞች አበሉ ሊከፈል የሚገባ መሆኑን ሲወስን እና ይህም ማስረጃ ቀርቦ በባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ወይም እሱ በሚወክለው ሰው ሲፈቀድ ብቻ ነው፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት የሚቀርብ ማስረጃ የአስቸጋሪ ሁኔታውን መጠን፣ ጉዳት ሊያደርስ የሚችልበትን የአካባቢ ሽፋን እንደ የርቀቱ የሚገልጽ፣ የስራ ሁኔታው ሊያደርስ የሚችለውን የጉዳት ደረጃ ከፍተኛ፣ መካከለኛ ወይም አነስተኛ ብሎ በመለየት የሚገልጽ መሆን አለበት፡፡

3. በስራ ሁኔታ አስቸጋሪነት ምክንያት የሚከፈል አበል ከገቢ ግብር ነፃ የሚሆነው አነስተኛ ጉዳት ለሚያስከትል የስራ ሁኔታ ከሠራተኛው የወር ደመወዝ ከ25%፣ መካከለኛ ጉዳት ለሚያስከትል የስራ ሁኔታ ከሠራተኛው የወር ደመወዝ ከ40%፣ ከፍተኛ ጉዳት ለሚያስከትል የስራ ሁኔታ ከሠራተኛው የወር ደመወዝ ከ60% ባልበለጠ መጠን ብቻ ነው፡፡

Ethiopian Ministry of Revenue
Records & Documentation N.2

4. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2 የተደነገገው ቢኖርም የጉዳቱን ደረጃ የሚለይ ማስረጃ ያልቀረበ ከሆነ ወይም የጉዳት ደረጃውን መለካት የማይቻል ከሆነ ከተቀጣሪው የወር ደመወዝ ከ25% ባልበለጠ መጠን ከገቢ ግብር ነጻ ይደረጋል።

## 9. በማንኛውም መስክ ለላቀ የስራ ክንውን የሚሰጥ ሽልማት፣

1. በአዋጁ አንቀጽ 65(1) ለላቀ የስራ ክንውን የሚሰጥ ሽልማት ከገቢ ግብር ነፃ ሲደረግ የሚችለው በሚከተሉት ሁኔታዎች የተሰጠ ሽልማት ሲሆን ብቻ ነው።

   ሀ. አንድን ቴክኖሎጂ በማሻሻል፣ አዲስ የፈጠራ ሥራ በመሥራት ወይም ወጪን ለመቀነስ የሚያስችል አሰራር ስራ ላይ በማዋል የሚሰጥ ሽልማት፣

   ለ. በአለም አቀፍ ደረጃ በሚደረግ ውድድር አገርን ወክሎ ወይም በአገር አቀፍ ደረጃ በሕግ በተቋቋመ የሽልማት ድርጅት በሚደረግ ማንኛውም ውድድር የሚሰጥ ሽልማት፣

   ሐ. በፌደራል፣ በክልል፣ በአዲስ አበባ ከተማ ወይም በድሬዳዋ አስተዳደር መንግስት የላቀ የስራ ክንውን ለፈፀመ ማንኛውም ግለሰብ ወይም ድርጅት የሚሰጥ ማንኛውም ሽልማት ሲሆን ነው።

2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1/ሀ/ የተመለከተው ሽልማት ከገቢ ግብር ነፃ ሲሆን የሚችለው ከፈጠራ ሥራው ጋር ግንኙነት ያለው አግባብነት ባለው የመንግስት አካል ለፈጠራው ሥራ እውቅና የተሰጠው ወይም የፈጠራ መብት ያገኘ ሲሆን ነው።

## 10. ለተቀጣሪ በነፃ የሚቀርብ ምግብ እና መጠጥ

1. በማዕድን ማውጣት፣ በማኑፋክቸሪንግ፣ በግብርናና ሆርቲካልቸር እንዲሁም በሆቴሎች፣ ሬስቶራንቶች እና የምግብ አገልግሎት ሥራ ላይ የተሰማራ ቀጣሪ ለተቀጣሪዎቹ በነፃ የሚያቀርበው ምግብ እና መጠጥ ከገቢ ግብር ነፃ ሊደረግ የሚችለው ቀጣሪው ያለልዩነት ለሁሉም ተቀጣሪዎች ነፃ የምግብና መጠጥ አገልግሎት የሚያቀርብ መሆኑ የተረጋገጠበት ሰነድ ወይም የሰራተኛ ማህበር መሪዎች ከድርጅቱ ጋር የተስማሙበት ሰነድ ሲቀርብ ብቻ ነው።

2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት ከግብር ነፃ የሚደረገው መጠጥ የአልኮል ይዘት ያለው ሲሆን አይችልም።

Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No. 2

## ክፍል ሶስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 11. በልዩነት ስለሚከፈል ግብር

ቀጣሪው በዚህ መመሪያ ከተወሰነው ገንዘብ በላይ ለተቀጣሪው የሚከፍል ከሆነ በብልጫ በተከፈለው ገንዘብ ላይ ግብር ይከፈልበታል።

### 12. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

አዋጁ ስራ ላይ ከዋለ በኃላ በእንጥልጥል ያሉ እና ውሳኔ ያላገኙ ጉዳዮች በዚህ መመሪያ መሰረት ውሳኔ ያገኛሉ።

### 13. የተሻረ መመሪያ

ከዚህ በታች የተዘረዘሩት መመሪያዎች ተሽረው በዚህ መመሪያ ተተክተዋል።

1. የኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለስልጣን ያወጣው የግብር ነፃ መብቶች መመሪያ ቁጥር 21/2001 እና መመሪያ ቁጥር 102/2007
2. በግብርና ልማት፣ ሆርቲካልቸር፣ በማዕድንና ነዳጅ ቁፋሮ እና በፋብሪካ ደረጃ በማምረት ተግባር ላይ የተሰማሩ ድርጅቶች ለሰራተኞቻቸው የሚያቀርቡት ነፃ የምግብ አገልግሎት ከገቢ ግብር ነፃ ለማድረግ የወጡ ሰርኩላር ደብዳቤዎች

### 14. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከሚያዝያ 1 ቀን 2011 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ መጋቢት 20 ቀን 2011 ዓ.ም

አህመድ ሺዴ
የገንዘብ ሚኒስትር

Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No. 2